# መድረክ

አብርሃም በየነ

ዕድሜውን በሙሉ ሲያነባ ለፈጀው
ካጋም መወዳጀት ለቁልቋል ምን በጀው?
ብሎ ለሚጠይቅ ያለን ተመክሮ
የመኢሶን መቆም ከደርግ ጋር አብሮ
በቀይ ሽብር እልቂት አንድ ትውልድ መትሮ
አጎብዳጅ ታሪኩን በደም አቆርፍዶ
እራሱን አጥፍቷል በራሱ ላይ ፈርዶ።

ያ ስህተት ለዛሬው ወይ ለወደፊቱ
ያለፍንበት ታሪክ አስተምሮነቱ
አቅጣጫ አመላካች እንዳይሆን መልዕክቱ
ታሪክ እንድትደግም እራሷን መልሳ
መድረክ ተቋቁሟል ለፍራሽ ዕደሳ።

መስከረም 2005